Seattle Office of Economic Development

# የመደብር የፊት ለፊት ጥገና የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ጥያቄዎች

## *መግቢያ*

የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት (OED) በሲያትል ከተማ ውስጥ ለግለሰብ፣ ለንግድ እና ለማህበረሰብ የኢኮኖሚ ዕድገት እድሎች ክፍት መዳረሻ እንቅፋቶችን የሚያፈርስ ስልታዊ መዋዕለ ንዋዮችን በማድረግ እና ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚ ለመገንባት ቁርጠኛ ነው። OED የሚያተኩረው በ:

- በሰው ሃይላችን ላይ ኢንቨስት ማድረግ እና ተሰጥኦን ከእድል ጋር ማገናኘት፣
- ለአነስተኛ፣ በሴቶች እና አናሳ ቡድኖች ለተያዙ ንግድ ድርጅቶቻችን ድጋፍ መስጠት እና የስኬት እንቅፋቶችን ማስወገድ፣
- በንብረት ባለቤትነት በኩል የሀብት ፈጠራ እድሎችን መክፈት፣
- በንግድ ቀጠናዎች ውስጥ በሚደረጉ የመዋዕለ ንዋዮች ሰፈሮችን ማደስ፣ እና
- በቁልፍ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ንግዶችን ማሳደግ።

**ማመልከቻዎን ከመጀመርዎ በፊት እባክዎ ልብ ይበሉ:**

- የጀመሩት መረጃዎን ማስቀመጥ (save) እና በኋላ ተመልሰው መጨረስ አይችሉም።
- በአንድ ጊዜ ሙከራ (ከ20-30 ደቂቃዎች ይወስዳል) ማመልከቻውን ለማጠናቀቅ ይዘጋጁ። ከመጀመርዎ በፊት እባክዎን የንግድ መረጃን እና የፋይናንስ ስራ ያዘጋጁ።
- ሁሉንም ጥያቄዎች አስቀድመው ለማየት የማመልከቻ መመሪያውን መጠቀም ይችላሉ።

**<u>ዝቅተኛ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት መስፈርቶች</u>**

ለመደብር የፊት ለፊት ጥገና ፈንድ ስጦታ ብቁ ለመሆን ንግድዎ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- በኮቪድ-19 ምክንያት ቀጥተኛ የኢኮኖሚያዊ ችግር ያጋጠማቸው።
- አሁን ላይ የሚሰራ/ቀኑ ያላለፈበት የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው።
- የከተማ የንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮችን ሙሉ በሙሉ የከፈሉ።
- ሁሉንም የፌዴራል፣ የክልል እና የከተማ ህጎች እና ደንቦችን ያከበሩ።
- በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ ያሉ።
- ከሁለት (2) የማይበልጡ ቦታዎች/ አድራሻ ያላቸው።
- ከጥር 1 ቀን 2021 ጀምሮ 50ወይም ያነሱ የሙሉ ጊዜ ተመጣጣኝ (FTE) ሰራተኞች ያላቸው (ለመፈተሽ ይህንን የ FTE ማስያ ይጠቀሙ)።
- ለሲያትል ከተማ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በ2020 እና 2021 በንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮች ላይ ሪፖርት በተደረገው መሰረት ንግዱ ከ$1,000 ዶላር በላይ እና ከ $7,000,000 ዶላር የማይበልጥ ዓመታዊ የተጣራ ገቢ ያለው መሆን አለበት።
- ከጥቅምት 1 ቀን 2022 ወዲህ ቢያንስ ለ24 ወራት በንግድ ላይ የቆዩ።
- በግል ባለቤትነት የተያዘ፣ በሌላ የንግድ ፈቃድ ስም ያልሆነ (non-franchise) እና ባለ ብዙ ቅርንጫፍ (non-chain) ንግድ ያልሆነ።
- ከጥር 1 ቀን 2021 በኋላ በመደብራቸው የፊት ለፊት ገጽታ ላይ አካላዊ ጉዳት ደርሶ ከሆነ።
- ለትርፍ የተቋቋመ ንግድ የሆነ።
- በአሁኑ ጊዜ ክፍት እና ንግድ ስራ እየሰራ ያለ።
- በአንድ ንግድ፣ የንግድ ድርጅት ባለቤት፣ EIN፣ SSN፣ UBI ቁጥር፣ የአንድ ንግድ ፈቃድ ቁጥር፣ የቤት እና/ወይም የንግድ አድራሻ ከሁለት በላይ ማመልከቻዎች መቅረብ አይችሉም። እያንዳንዱ ማመልከቻ ለተለያዩ ክስተቶች እና የተለያዩ ቀናት ያላቸው መሆን አለባቸው።
- ከአካላዊ ቦታ እና/ወይም ከተንቀሳቃሽ የጭነት መኪና ሰፊውን ህዝብ እያገለገለ ያለ።

**ብቁ <u>ያልሆኑ</u> ንግዶች:**

- 501(c)(3), 501(c)(6) ወይም 501(c)(19) ለትርፍ ያልተቋቋሙ አካላት።
- ንግዱ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የኪራይ ወይም የመዋዕለ ንዋይ ንብረት (የግል ቤት/ መሬት አሻሻጭ፣ ገለልተኛ የግል ቤት/ መሬት አሻሻጮች፣ የአጭር ጊዜ ኪራዮች አየርቢንቢ (Airbnb)፣ ቪርቦ (Vrbo)፣ ወዘተ ያካታቱ)።
- ታክሲዎች፣ የተሳፋሪ መጋራቶች፣ ወይም የምግብ ማድረስ አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ Uber፣ Lyft፣ Yellow Cab፣ Door Dash፣ Uber Eats፣ ወዘተ)።
- የሀሺሽ ዕጽ (Cannabis) ሱቆች፣ አምራቾች እና ማከፋፈያዎች።
- "የአዋቂዎች መዝናኛ" [በሲያትል ማዘጋጃ ቤት ህግ 6.270 ላይ እንደተገለጸው።]
- ከ ኪንግ ካውንቲ ጋር ባልተካለለ አካባቢ ውስጥ የሚገኝ የንግድ ተቋም።

## ብቁነት

1. **ለዚህ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ የሚያመለክቱ የንግዱ ባለቤት ነዎት?**
   - አዎ
   - አይ

2. **ለመደብር የፊት ለፊት ጥገና ፈንድ ሲያመለክቱ ይህ የመጀመሪያዎ ነው?**
   - አዎ
   - አይ

3. **ለሁለተኛ የጥገና ችግር እያመለከቱ ነው? (ክስተቶች በሁለት (2) የተለያዩ ቀናት ውስጥ የተከሰቱ መሆን አለባቸው እና ንግዶች ሊቀበሉ የሚችሉት ቢበዛ ሁለት (2) ስጦታዎች ብቻ ነው)**
   - አዎ
   - አይ

4. **ለቋንቋ እርዳታ አስተርጓሚ ይፈልጋሉ?**
   - አዎ
   - አይ

5. **ሰነዶች እንዲተረጎሙልዎት ይፈልጋሉ?**
   - አዎ
   - አይ

6. **ንግድዎ በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ ይገኛል?**
   - አዎ
   - አይ

7. **ንግድዎ ስንት ቦታዎች አለው?**
   - 1
   - 2
   - 3 ወይም ከዚያ በላይ

8. **ከጥር 1 ቀን 2021 በኋላ በማንኛውም ጊዜ ንግድዎ ከ50 በላይ የሙሉ ጊዜ ተመጣጣኝ ተቀጣሪዎች (FTEs) ኖሮታል/ አሉት?**
   - አዎ

- አይ

**9. ለሲያትል ከተማ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በ2020 እና 2021 በንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮች ላይ ሪፖርት በተደረገው መሰረት ንግዱ ከ$1,000 ዶላር በላይ እና ከ $7,000,000 ዶላር የማይበልጥ ዓመታዊ የተጣራ ገቢ ያለው መሆን አለበት።**

- አዎ
- አይ

**10. ንግድዎ ትክክለኛ የሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃድ አለው?**

- አዎ
- አይ

**11. የከተማ ንግድ እና ስራዎች (B&O) ግብሮችዎ የተሟሉ ናቸው?**

- አዎ
- አይ

**12. እስከ ጥቅምት 1 ቀን 2022 ድረስ ንግድዎ ቢያንስ ለ24 ወራት ሲሰራ ነበር?**

- አዎ
- አይ

**13. ንግድዎ ከ COVID-19 አሉታዊ የገንዘብ ተፅእኖ ገጥሞታል ወይም በዋሽንግተን ስቴት/ ግዛት "ቤት ይቆዩ፣ ደህንነትዎን ይጠብቁ" ወይም "ደህንነቱ የተጠበቀ ጅምር" እንደገና ለመከፈት መስፈርቶች ምክንያት በተወሰነ አቅም እንዲሠራ ተገዷል?**

- አዎ
- አይ

**14. ንግድዎ ለትርፍ ያልተቋቋመ ንግድ ነው?**

- አዎ
- አይ

**15. ዋና የንግድ የሥራ ምድብ**

- አስተዳደራዊ አገልግሎቶች (የአስተዳደር ድጋፍ አገልግሎቶች)
- ግብርና ወይም የተፈጥሮ ሀብቶች (የደን ልማት፣ እርሻ ማረስ፣ ማዕድን፣ ዓሳ ማጥመድ)
- የንግድ አገልግሎቶች (ሕጋዊ፣ የሂሳብ ሥራ፣ ግብይት፣ ለንግዶች ማማከር)
- የሕፃናት እንክብካቤ ወይም መዋዕለ ሕጻናት
- የግንባታ ወይም ከባድ የጣቢያ ሥራ (ሥራ ተቋራጮች፣ ከባድ ሲቪል፣ መኖሪያ)
- የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች (ፊልም፣ የምሽት ህይወት፣ ልዩ ዝግጅቶች፣ ፎቶግራፊ፣ ማስታወቂያ፣ ግራፊክ ዲዛይን፣ ይዘት መፍጠር፣ ፋሽን፣ አልባሳት እና ጨርቃ ጨርቅ፣ ስነ ጽሑፍ፣ ህትመት፣ ጋዜጠኝነት፣ የቅጅ አርትዖት፣ የኪነጥበብ እና የባህል ተቋማት እና የምሽት ህይወት ቦታዎች)
- የትምህርት አገልግሎቶች (ስልጠና፣ የርቀት ትምህርት)
- ፋይናንስ፣ ኢንሹራንስ ወይም የርስት/ ቤቶች ሀብት (ባንኮች፣ የመዋዕለ ንዋይ ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ደላሎች፣ የርስት/ የቤት ሀብቶች ደላሎች)
- የምግብ አገልግሎቶች: መጠጥ ቤቶች ወይም የመጠጥ ቤቶች

- የምግብ አገልግሎቶች: ምግብ ቤቶች
- የጤና እንክብካቤ (የሕክምና ቢሮዎች፣ ክሊኒኮች፣ የአዛውንቶች ማስታመሚያ ቤቶች፣ የመታሸት አስታማሚዎች/ ቴራፒስቶች፣ የጥርስ ሐኪሞች)
- መስተንግዶ (ሆቴሎች)
- የሕይወት ሳይንስ ወይም የስነ ሕይወት ተክኖሎጂ (biotech) (ምርምር እና ልማት፣ የመድኃኒት አምራቾች፣ የህክምና መሣሪያዎች)
- ማምረት፡ የስነ በረራ (የበረራ ምርት አቅራቢዎች)
- ማምረት፡ የምግብ እና የመጠጥ ምርት (የምግብ አምራቾች፣ የባህር ምግብ ማቀነባበሪያዎች፣ ቢራ ፋብሪካዎች፣ የወይን ጠጅ አምራቾች፣ የአረቄ ማምረቻዎች)
- ማምረት፡ የባህር/ የመርከብ (የመርከብ እና የጀልባ ግንባታ እና ጥገና)
- ማምረት፡ ሌላ
- የግል አገልግሎቶች (ውበት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ የሕጻናት እንክብካቤ፣ ደረቅ ጽዳት፣ የግል ወይም የሸማች አገልግሎቶች፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ/መዝናኛ የቤት ውስጥ እንቅስቃሴ ቦታዎች፣ ቦውሊንግ መጨወቻዎች፣ ጂሞች፣ የጨዋታ መገልገያዎች፣ ወዘተ.)
- የጽሑፍ ማተሚያ ወይም ሌላ መረጃ (ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጽሐፍ ማተም፣ የተንቀሳቃሽ ፊልም ምርት)
- ሙያዊ ወይም ቴክኒካዊ አገልግሎቶች (የስነ ሕንፃ ድርጅቶች፣ የምህንድስና ኩባንያዎች)
- የችርቻሮ ንግድ: መደብር
- ችርቻሮ ንግድ: መደብር ያልሆነ ወይም ኢ-ኮሜርስ (የመስመር ላይ ንግድ)
- ማህበራዊ አገልግሎቶች (የተቋማት የምግብ አገልግሎቶች፣ መኖሪያ ቤት፣ የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎቶች፣ የማህበራዊ ሥራ)
- ሶፍትዌር (Software) (የኮምፒዩተር ፕሮግራም፣ በደመና ላይ የተመሰረቱ (cloud-based) ምርቶች እና አገልግሎቶች፣ ወይም የቴሌ ግንኙነቶች (ሶፍትዌር፣ ኮምፒዩተይ ክላውድ (cloud) ማስላት፣ የበይነመረብ አቅራቢዎች፣ የቴሌኮም አቅራቢዎች)
- መጓጓዣ ወይም የመጋዘን ሥራ (የጭነት መጓጓዣ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የጭነት ማስተላለፍ፣ አየር መንገዶች፣ ማከማቻዎች፣ የመሬት ማጓጓዣ፣ መልእክት አመላላሾች)
- መጓጓዣ: በውሃ ላይ (መርከቦች፣ በውሃ ላይ የተመሠረቱ ጉብኝቶች፣ ጭነት)
- የቆሻሻ አገልግሎቶች (የቆሻሻ ሥራ ማካሄድ)
- የጅምላ ሻጮች፣ የጅምላ ነጋዴዎች

**16. ንግድዎ የምግብ መኪና ነው?**

- አዎ
- አይ

**17. ንግድዎ ከአንድ አካላዊ/ ተጨባጭ ሥፍራ ይሠራል?**

- አዎ
- አይ

**18. ይህ አካላዊ ሥፍራ ከእርስዎ ከሚኖሩበት ሰፈር ይለያል?**

- አዎ
- አይ

**19. ንግድዎ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የኪራይ ወይም የመዋዕለ ንዋይ ንብረት ነው?**

- አዎ
- አይ

**20. ንግድዎ አንድ ታክሲ፣ ተሳፋሪ የሚጋሩት፣ ወይም የምግብ ማቅረቢያ አገልግሎት ነው (እንደ ኡበር፣ ሊፍት፣ ቢጫ ካቢ፣ የዶር ዳሽ የመሳሰሉ)?**
- አዎ
- አይ

**21. በሲያትል ማዘጋጃ ቤት የሕግ አንቀጽ 6.270 መሠረት ንግድዎ እንደ "የአዋቂ መዝናኛ" ንግዶች ቁጥጥር ይደረግበታል?**
- አዎ
- አይ

## የንግድ መረጃ

**22. የንግድ ስም**
**22. የንግድ DBA (እንደ ንግድ ሥራ መጠሪያ)**
**23. የተዋሃደ የንግድ መለያ (UBI) ቁጥር**
**24. የሲያትል የንግድ ፈቃድ የታክስ ምስክር ወረቀት ቁጥር**
**25. UEI (ልዩ የሆነ አካል መለያ) ቁጥር**
**26. እራስዎን ጨምሮ፣ ንግድዎ ጠቅላላ ስንት ሠራተኞች (የከፊል ሰዓት እና የሙሉ ጊዜ) አለው?**
**27. ሁሉም የተቀጠሩ ሠራተኞች (የንግድ ባለቤቱን ጨምሮ) በሳምንት ስንት ሰዓታት ይሠራሉ?**

## ዋና የንግድ ቦታ/ አድራሻ

**28. እባክዎን ዋና ንግድዎ ያለበትን ቦታ ያስገቡ:**
- አድራሻ
- አድራሻ 2
- ከተማ
- ግዛት (ስቴት)
- ዚፕ ኮድ

**29. የንግዱ የመላላኪያ አድራሻ (ከላይ ካለው ቦታ የተለየ ከሆነ)**
- አድራሻ
- አድራሻ 2
- ከተማ
- ግዛት (ስቴት)
- ዚፕ ኮድ

## የንግድ ባለቤት ዝርዝሮች

**ጽ/ቤታችን የዚህን የእርዳታ ማመልከቻ በተመለከተ ስላሉ ዝመናዎች እርስዎን እና ንግድዎን ለማነጋገር (ለማግኘት) ከዚህ በታች የቀረበውን መረጃ ይጠቀማል። ከዚህ በታች የገባው መረጃ የሚሠራ/ ገባሪ መሆኑን እባክዎ ያረጋግጡ።**

**30. የመጀመሪያ ስም**
**31. የአያት ሥም**

**32. ስልክ ቁጥር**
**33. የስልክ ቁጥሩን ያረጋግጡ**
**34. ኢሜይል**
**35. ኢሜይል ያረጋግጡ**
**36. በቤት ውስጥ የሚነገር የመጀመሪያ ቋንቋ**

**ሌላ**

**37. እርስዎ የሂስፓኒክ ወይም የላቲኖ/ና/ኒክስ ተወላጅ ነዎት?**
**38. ዘርዎ ምንድነው?**

- ነባር ተወላጅ አሜሪካዊ ወይም የአላስካ ተወላጅ
- ኤስያዊ
- ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ
- ተወላጅ ሃዋያዊ ወይም የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ
- ነጭ
- የመካከለኛ ምስራቅ ተወላጅ ወይም ሰሜን አፍሪካዊ
- ሌላ
- ላለማለት እመርጣለሁ

- **በየትኛው የእስያ የዘር ንዑስ ምድብ ወይም ንዑስ ምድቦች ተለይተው ይታወቃሉ?**
  - ቻይናዊ
  - ካምቦዲያዊ
  - ፊሊፒኖ
  - ሀሞንግ ተወላጅ
  - ሕንዳዊ
  - ጃፓናዊ
  - ኮሪያዊ
  - የላኦስ ተወላጅ
  - የታይ ተወላጅ
  - ቬይትናማዊ

- **በየትኛው የሃዋይ እና የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ የዘር ንዑስ ምድብ ወይም ንዑስ ምድቦች ተለይተው ይታወቃሉ?**
  - ቻሞሮ
  - ጉዋማናዊ
  - የሃዋይ ተወላጅ
  - ፖሊኔዥያዊ
  - የሳሞአን ተወላጅ

- **በየትኛው የጥቁር ዘር ንዑስ ምድብ ወይም ንዑስ ምድቦች ተለይተው ይታወቃሉ?**
  - አፍሪካዊ አሜሪካዊ
  - አማራ
  - ኤርትራዊ
  - ኦሮሞ
  - ትግራዋይ
  - የሶማሊ ተወላጅ
  - ምዕራባዊ አፍሪካዊ

- **በየትኛው የመካከለኛው ምስራቅ ወይም የሰሜን አፍሪካ የዘር ንዑስ ምድብ ወይም ንዑስ ምድቦች እርስዎ ተለይተው ያታወቃሉ?**
    - አልጄሪያዊ
    - ግብፃዊ
    - ኢራናዊ
    - ሊባኖሳዊ
    - ሞሮኮአዊ
    - ሶሪያዊ

- **በየትኛው የሂስፓኒክ ንዑስ ምድብ ወይም ንዑስ ምድቦች ተለይተው ያታወቃሉ?**
    - ኩባዊ
    - ጓተማላዊ
    - ሳልቫዶራዊ
    - ሜክሲካዊ
    - ፖርቶ ሪካዊ

**39. ጾታዎን እንዴት ይገልፁታል?**

- ወንድ (የጾታ ልውውጥ ያደረጉ ወንዶችን ጨምሮ)
- ሴት (የጾታ ልውውጥ ያደረጉ ሴቶችን ጨምሮ)
- ላለማለት እመርጣለሁ
- ራስን እንደ ... መግለፅን እመርጣለሁ
- ሁለትዮሽ ያልሆነ
- ቋሚ ጾታ የሌለዉ
- ጾታ አልባ

**እባክዎን ይግለጹ:**

**40. ንግዱ ስንት ባለቤቶች አሉት?**

**41. ተጨማሪ የንግድ ባለቤቶች**

## ጉዳት

**42. እኔ (የንግዱ ባለቤት) የንግዴን የሲያትል ከተማ የንግድ እና የሥራ (B&O) የግብር ፋይል መረጃን ቅጂዎች እንዲያገኙ፣ እንዲገመግሙና እንዲያፀድቁ ለኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት ፈቃድ እሰጣለሁኝ።**

- የንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮችዎን በተግባር አሟልቶ ለመገኘቱ ማረጋገጫ የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) ለማረጋገጥ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

**43. የገንዘብ ድጋፍ እየጠየቁለት ያሉት ክስተት የተከሰተበት ቀኑ ስንት ነበር?**

**44. በዚህ ክስተት የእርስዎ ንግድ በገንዘብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮበታል?**

- አዎ
- አይ

**45. በእርስዎ የመደብር ፊት ላይ የደረሰውን ጉዳት በተሻለ የሚገልጸው ምንድን ነው?**

- የተሰበረ መስኮት
- የበር ጉዳዮች
- ሌላ

**46. ያለአግባብ ቅቦች/ ጽሁፎች ለግራፊቲ ማስወገጃ እያመለከቱ ነው?**

- አዎ
- አይ

**47. በሱቅ ፊት ለፊቱ ላይ የደረሰው ጉዳት አስቀድሞ ተስተካክሏል? (እባክዎ ደረሰኞችዎን ለማቅረብ ዝግጁ ይሁኑ።)**

- አዎ
- አይ

**48. በእርስዎ ደረሰኞች ላይ በመመስረት፣ በመደብርዎ ፊት ለፊቱ የደረሰ ጉዳት ምን ያህል ነው?**

**49. ስለዚህ ክስተት የፖሊስ ሪፖርት ለሲያትል ፖሊስ መምሪያ አስገብተዋል?**

- አዎ
- አይ

**50. የፖሊስ ሪፖርት ቁጥርዎ ስንት ነው?**

**51. ንግድዎ ከሲያትል ታሪካዊ ጥበቃ ቀጠናዎች በአንዱ ውስጥ ነው ( እዚህ ይመልከቱ)?**

- አዎ
- አይ

**52. በታሪካዊ ጥበቃ ቀጠናዎች ውስጥ ባሉ ሕንፃዎች ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ጥገናዎች የተጐራባቾች መምሪያ የምስክር ወረቀት ማጽደቂያ እንደሚያስፈልገው ለማወቅ አንድ ከቀጠናዉ አስተባባሪ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት እንዳለበት ተረድቻለሁ። የታሪክ ጥበቃ ቦርድ ማፅደቅ ካስፈለገ፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት አንድ የምስክር ወረቀት ማረጋገጫ ይወጣል።**

- አዎ
- አይ

## የንግድ እገዛ

**53. በኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) እና በአጋሮቹ ከሚሰጡት ከሚከተሉት የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮግራሞች ውስጥ ንግድዎ ከማንኛቸውም ተጠቃሚ ይሆናልን?**

- የማህበራዊ ሚዲያ፣ የድህረ ገጽ ንድፍ እና የኢ-ኮሜርስ የመረጃ ማወቅ ሀብቶችን ጨምሮ የዲጂታል ትምህርት
- የህግ አገልግሎቶች
- ከከተማው የCOVID የማወቅ ሀብቶች ምንጮች ጋር ማገናኘት
- ፈቃድ መስጠት እና የንግድ ደንቦች አገልግሎቶች
- የሽያጭ መለዋወጫ ነጥቦች ስርዓት
- የሰፈር ዉስጥ ንግድ ማሻሻያ ድርጅት ማግኘት
- መንገድ የማጽዳት እና የማዋብ ማወቅ ሀብቶች ምንጮች
- የሂሳብ አያያዝ እና የፋይናንስ ትምህርት ማወቅ ሀብቶች ምንጮች

- የግንባታ ተጽዕኖ እገዛ
- በውስጠ ቋንቋ ማዳረስ እና እርዳታ
- የምግብ ቤት እና የምግብ ንግድ ድጋፍ (የተስፋፋ የፈቃድ አሰጣጥ አማራጮችን እንዳለ መያዝ፣ የመሸፈኛ መላኪያ መተግበሪያ ክፍያዎችን ወይም የቀለለ የማሟላት ሂደቶችን)
- የንግድ ሥራ ማቀድ
- ሌላ ተጨማሪ እርዳታ አያስፈልግም
- ሌላ

**54. ከ COVID-19 ጋር የተዛመደ ማንኛውንም የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋልን? የሚመለከተውን ሁሉ ምልክት ያድርጉበት**

- የደመወዝ መከላከያ ፕሮግራም (PPP)
- የኢኮኖሚ ጉዳት የአደጋ ብድር (EIDL)
- የምግብ ቤት መልሶ ማቋቋም የድጋፍ ገንዘብ (RRF)
- የተዘጋ የመድረክ አንቀሳቃሾች የዕርዳታ ገንዘብ ስጦታ (SVOG)
- የከተማ ማረጋጊያ የዕርዳታ ገንዘብ ስጦታ
- የኪንግ ካውንቲ የኮቪድ ማቃለያ የድጋፍ ገንዘብ
- የበጎ አድራጎት ወይም የግል-ዘርፍ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ
- የዋሽንግተን ስቴት የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ
- የየስኮላርሺፕ ጃንኪስ (Scholarship Junkies) መጠጥ ቤቶች እና ምግብ ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ
- ሌላ
- ምንም

**55. ከገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ሌላ በተጨማሪ ከ COVID-19 ጋር የተዛመደ ንግድዎ ምን ዓይነቶች ሌሎች የገንዘብ ድጋፍ ሊፈልግ ይችላል?**

- የሂሳብ አያያዝ
- የአቅርቦት ሰንሰለት አስተዳደር
- ብድሮች
- የፌዴራል ብድር ዕርዳታ (የደመወዝ ከለላ ፕሮግራም፣ የኢኮኖሚ ጉዳት የአደጋ ብድር፣ ወዘተ)
- ሌላ
- ምንም

**56. ንግድዎ አዲስ ድህረ ገፅ ይፈልጋል?**

- አዎ
- አይ

**57. በአሁኑ ጊዜ የየሽያጭ መለዋወጫ ነጥብ ስርዓት (ለምሳሌ: Toast፣ Square፣ Shopify) ይጠቀማሉ?**

- አዎ
- አይ

**58. ንግድዎ በመስመር ላይ ምርቶችን ይሸጣል?**

- አዎ
- አይ

**59. ንግድዎ ከመንገድ ዳር የሚነሳ የንግድ ሥራ ይሠራል?**
- አዎ
- አይ

**60. ንግድዎ በYelp ላይ አለ?**
- አዎ
- አይ

## የምስክር ወረቀቶች

**61. ስለዚህ የዕርዳታ ስጦታ እንዴት ሰሙ?**
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) ድህረ ገጽ
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) ብሎግ
- ማህበራዊ ሚዲያ
- የአነስተኛ ንግድ ምክር ቤት
- የንግድ ሥራ ማሻሻያ ማህበር
- የንግድ ድርጅት
- የአፍ ቃል
- ሌላ

**62. በዋሽንግተን ስቴት ሕጎች መሠረት በሐሰት ቅጣት እንድሚጠየቅ በመረዳት ከዚህ ቀደም ብሎ የተሰጠው ቃል እውነት እና ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ ወይም አውጃለሁ። የተሰጠው መረጃ ሁሉ ከሚመለከታቸው/ ከሚያገባቸው የስቴት ወይም የፌዴራል መንግስት ወኪል ድርጅቶች ሁሉ ጋር ይረጋገጣል። ይህ የሲያትል ንግድ እና ሥራ (B&O) የግብር አቅራቦት መረጃን ለመገምገም እና ለማረጋገጥ ፈቃድ መስጠትን ያካትታል። ይህንን ማመልከቻ ለእርዳታ ሲፈርሙ እና ሲያስገቡ፣ በኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት በንግድዎ የቀረበውን የግብር መረጃ እንዲያገኝ እና እንዲገመግመው ፈቃድ እየሰጡ ነው።**

**ይህንን የመደብር የፊት ለፊት ጥገና የድጋፍ ገንዘብ ማመልከቻ ስላጠናቀቁ እናመሰግናለን።**